የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ የካቲት ፳፪ ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 30
ADDIS ABABA 1st March 2004

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፺፯/፲፱፻፺፮ ዓ·ም
"የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ደንብ ........................ ገጽ ፪ሺ፭፻፹፱

## CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 97/2004
"Agricultural Mechanization Service Enterprise establishment Council of Ministers Regulation ........................................................ Page 2589

## የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ድርጅት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎትን ኮርፖሬሽንን በድርጅትነት እንደገና ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢ/ፌ/ዲ/ሪፑብሊክ የሕግ አስፈጻሚውን አካል ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯/፩/ሀ/ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፺፯/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>መቋቋም</u>

፩· የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪· ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

፫· <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF AGRICULTURAL MECHANIZATION SERVICE ENTERPRISE.*

It is found necessary to re-establish Agricultural Mechanization Service Corporation as an Enterprise.

Hence. This Regulation is issued by the Coouncil of Ministers pursuant to article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopian Proclamation No.4/1995 and Art-47/1/(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

   This Regulation may be cited as the "Agricultural Mechanization Service Enterprise establishment Council of Ministers Regulation No 97 /2004.

2. *Establishment*

   1) There is hereby established the Agricultural Mechanization Service Enterprise (hereinafter referred to as the "Enterprise") as a public Enterprise.
   2) The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

   The Public Enterprise's Supervisory Authority shall be the supervising authority of the Enterprise.

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል። እንደአስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፭. <u>ዓላማ</u>

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

፩. የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎትን በኪራይ መስጠት፣
፪. የእርሻ መሣሪያዎች የጥገና አገልግሎት በክፍያ መስጠት፣
፫. የእርሻ መሣሪያዎችንና መለዋወጫዎችን ከአገር ውስጥ እና ከውጭ ገዝቶ ለሽያጭ ማቅረብ፣
፬. የእርሻ መሣሪያዎችንና ተቀጽላዎችን በኪራይ ለተጠቃሚዎች መስጠት፣
፭. የምርትና የግብርና ግብአቶችን የማጓጓዝ አገልግሎት በኪራይ መስጠት፣
፮. የግብርና ቴክኖሎጂ የሽግግር ማዕከል ሆኖ በማገልገል ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎችን አጠቃቀም እንዲለመድ ማድረጋ፣
፯. የእርሻ መሣሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም ሥልጠናና የምክር አገልግሎት በክፍያ መስጠት፣
፰. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ።

፮. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፳ሚሊዮን ፭፻፹ሺ ፰፻፷፩ ከ፳፯ /ሃያ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰማንያ ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ አንድ ከሃያ ሰባት ሣንቲም /ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፲፩ሚሊዮን ፪፻፷፱ሺ ፪፻፩ ከ፳፯ /አሥራ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ አንድ ከሃያ ሰባት ሣንቲም/ በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል።

፯. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

፱. <u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

በአዋጅ ቁጥር ፫፻፴፯/፲፱፻፹፯ የተቋቋመው የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ኮርፖሬሽን መብትና ግዴታ በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፏል።

፲. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት
ጠቅላይ ሚኒስትር

4. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. *Objectives*

The objectives for which the Enterprise is established shall be,–

1) To render agricultural mechanization services on rental bases:
2) To render agricultural machinery maintenance services on rental bases:
3) Making available for sale farm implements and spare parts from home and abroad:
4) Giving agricultural machirieries and implements on rental bases;
5) To render farm produce and farm inputs transportation services on rental bases:
6) To introduce the utilization of modern farm implements by being the transmission belt of modern agricultral technology;
7) Providing Training and Consultation Service on a better and effective utilization of farm machines in consideration:
8) To engage in any other related activities necessary for the attainment of its purposes.

6. *Capital*

The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 20.580.861.27 (Twenty million five hundred eighty thousand eight hundred aixty one and cents twenty seven) of which Birr 11.269,201.27 (Eleven million two hundred sixty nine thousand two hundred one and cents twenty seven) is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

8. *Duration*

*The Enterprise is established for an indefinite duration.*

9. *Transfer of Rights and Obligations*

The rights and obligations of Agrcultural Mechanization Service Corporation established by Proclamation No.337/87 are hereby transferred to the Enterprise.

10. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in The Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 1st day of March 2004

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLICE OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE